የሴቶችን መገረዝ የሚፈቅድም ሆነ የሚፈጽም በሕግ ይከሰሳል።
ለ እሥራት ያበቃል።

- መገረዝን በተመለከተ መተባበር አይፈቀድሉትም
- ግርዘት እንዲከናወን ዕድልን መስጠት አይፈቀ ድሉትም፤
- ማመቻቸት አይፈቀድሉትም፥ ለምሳሌ ለግርዘቱ ክንውን ገንዘብን መክፈል።
- ሰው እንዲገረዝ ትዕዛዝ ማስተላለፍ አይፈቀድሉ ትም።

በሆላንድ አገር ውስጥ፥ እያንዳንዱ ሕፃን የመጠበቅ መብ ት ስላለው፥ ይህም የጤንነትን ጥበቃ ያካትታል፥ ሴቶችን መግረዝ ወንጀል ነው። ሴቶችን መግረዝ የሴቶችን ጤንነ ት ይጎዳል።

መረጃዎችን ከ "ፋሮስ የትኩረት ነጥብ፥ የሴቶች መገረዝ" (Focalpoint meisjesbesnijdenis van Pharos) ማግኘት ይችላሉ፤
በቴሌፎን በሥራ ቀኖች ከ12.00 ሰዓት እስከ 17.00 ሰዓት ድረስ ጥያቄን ሁሉ ይቀበላሉ። ቴሌ. ቁጥር 030-2349800
ኢሜይል፥ focalpointmeisjesbesnijdenis@pharos.nl
FSAN,(ኤፍ.ኤስ.አ.ኤን) ሰኞና ሓሙስ በቴሌፎን መረጃዎች ን ከ11.00 ሰዓት እስከ 16.00 ሰዓት ማግኘት ይቻላል፤
ቴሌ ቁጥር፥ 020-4869157 ወይም 06-52123594
ኢሜይል፥ info@fsan.nl ወይም z.naleie@planet.nl

ለጥያቄም ሆነ ለእርዳታ የሚቀጥለውን አድራሻ ይጠቀሙ፥

# የሴቶች ግርዘት

# ወላጆቼ እምቢ ይላሉ



የሴቶችን መገረዝ በተመለከተ ከወጣቶች የጤና ጥበቃ ቡ
ድን ሓኪም ወይም አስታማሚ ጋር፥ በመጠየቂያ ጽሕፈት
ቤት ወይም በኼኼዴ (GGD) ስትነጋገሩ ነበር፤
ይህን፥ በራስዎ ቋንቋ የተጻፈውን ወረቀት ለእርስዎ የምን
ሰጥበት ምክንያት፥ በንግግራችሁ ጊዜ ያገኙትን መግለጫ
እንደገና ከቤተ ሰብዎ፥ ከዘመዶችዎ ወይም ከጓደኞችዎ ጋ
ር በጥሞና ማንበብ እንዲችሉ ነው።

በዓለም ከ130 ሚሊዮን በላይ ልጃገረዶችና ሴቶች በግርዘት
ተጠቅተዋል። ይህ ጉዳይ በ28 የአፍሪካ ሃገሮች፥ በኤሺያና
በመካከለኛው ምሥራቅ በሚገኙ አንዳንድ ብሔሮች ዘንድ
ይዘወተራል።
ለምሳሌ፤ በሶማሊያ፥ በጂቡቲ እና በሰሜን ሱዳን፥ ሴቶቹ
ሁሉ ለማለት ይቻላል፥ የከፋው የመግረዝ ዓይነት "infibu
latie" ወይም ፈርኦናዊ ግርዘት የተባለ፥ ይፈጸምባቸዋል።
ብዙዉን ጊዜ የሚገረዙት ልጃገረዶች ናቸው። እንደየአገሩ
ትክክለኛው ዕድሜአቸው ይለያያል፤ ነገር ግን ብዙዉን ጊ
ዜ መገረዙ የሚፈጸመው ከመጀመሪያው የወር አበባቸው
በፊት ነው።
አንድ ሴትልጅ ለምን መገረዝ እንዳለባት የተለያዩ ምክን
ያቶች ይሰጣሉ። ለምሳሌ፥ ደንባችንና ሥርዓታችን ስለሆነ፤
ድንግልናን ይጠበቃል፥ የጋብቻን ዕድል ያሰፋል፥ ወይም
በእስላም ሃይማኖት ደንብ ነው፤ ይባላል።

*የዓለም የጤና ጥበቃ ድርጅት(WHO) ሓኪሞቹንና በሕክምና
የሚደግፉትን ሠራተኞቹን ሁሉ የሴቶችን ግርዘት እንዳያከ
ናውኑና፥ የጤና ጥበቃ ድርጅቶች መሣሪያዎችንም ግርዘት
ን ለማከናወን እንዳያቀርቡ አዛቸዋል።*

*በዓለም ዙሪያ ሰዎች የሴቶችን መገረዝ በመቃወም እምቢ
እያሉና ይህን ተግባር ለማስቆም በትጋት እየተሠሩ ናቸው
።*

# የሴት ልጅዎን መገረዝ በተመለከተ እምቢ ይበሉ ምክንያቱም፤

- ያለ ማደንዘዣ፥ ከመጠን በላይ የሚያም ስለሆነ
፤
- አስደንጋጭ ልምምድ ስለ ሆነ፤
- በጣም ብዙ ደም ሊፈስስ ስለሚችል፤
- የማመርቀዝ ዕድል ስላለ፥
- ሞትን ሊያስከትል ስለሚችል፤
- ከማህፀን ማመርቀዝ የተነሳ መኻንነትን ሊያስከ
ትል ስለሚችል፤
- ሥጋዊ ግነንኙነትን (በጋብቻ ሌሊት) አስቸጋሪ
ስለሚያደርገው፤
- መውለድን አስቸጋሪ ስለሚያደርገው፤
- ሥር የሰደደ ሥቃይ በአንጀት ውስጥ ሊመጣ
ስለሚችል፤
- የወር አበባን በተመለከተ ችግሮች ሊነሡ ስለሚ
ችሉ፤
- በሽንት መተላለፊያ ችግሮች፥ በሚሸናበት ጊዜ
ችግሮች ሊፈጠሩ ስለሚችሉ፤
- በእስልምናም ሆነ በክርስትና፥ ሴቶችን መግረዝ
ያልታዘዘ ስለሆነ፤

በሆላንድ አገር በሕግ የተከለከለ ስለሆነ።

# ድንጋጌ በሆላንድ

ከ 1993 ዓ ም ጀምሮ ሴቶችን መግረዝ በሆላንድ
በሕግ የተከለከለ ነው።
ይኸም ማንኛውንም የመግረዝን ዓይነት ያካትታል፤

- ቂንጥርን መውጋት ወይም መሰንጠቅ፤ (Incisie)
- ቂንጥርን ፈጽሞ መቁርጥ፥(Clitoridectomie)
- ቂንጥርንና እንዲሁም፥ በከፊልም ሆነ በጠቅላላ፥ የ
እምስን ንኡስ ከንፈሮች ቆርጦ ማስወገድ፤(Excisie)
- ቂንጥርንና ትናንሹንም ሆነ ትላልቁን የእምስ ከንፈ
ሮችን ቆርጦ ማስወገድ። (Infibulatie)